# ለጥፋት ድምፆች ጆሮውን የነፈገ ህብረት

**ታሪኩ በዛብህ** 5/4/12

ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ግብፅን ሲመሩ የኖሩት የቀድሞው የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ የአባይ ወንዝ ጉዳይን በአገሪቱ ውስጥ የሚነሱ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ለመሸፋፈን ዓላማ ሲጠቀሙበት ኖረዋል፡፡ ሙባረክ ግብፃዊያን ከአባይ ወንዝ ውጭ ህይወት የላቸውም፤ ከአባይ ጋር በተያያዘ ግብፅና ግብፃዊያን አደጋ ውስጥ ናቸው በሚል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የአገሪቱን ዜጎች በስጋትና በጥርጣሬ ውስጥ እንዲጠመዱ አድርገው ቆይተዋል፡፡ የቀድሞው የአገሪቱ አስተዳደር ኢትዮጵያ ይህንን ውሃ ጥቅም ላይ በማዋል የግብፃዊያን ህልውና አደጋ ላይ የመጣል ግብ አላት የሚል እውነተኝነት የራቀውን ስብከት በመንዛትም ግብፃዊያን በኢትዮጵያ ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዲፈጥሩ አድርጓል፡፡ ከዚህም አልፎ የቀድሞው የግብጽ መንግስት ወንዙን በመጠቀም ልማት ለማካሄድ የሚሞክሩ የተፋሰሱ አባል አገራትን በተለይም ደግሞ የወንዙ ውሃ መነሻ የሆነችው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ድጋፍ እንዳታገኝ የተለያዩ ደባዎችንም ፈፅሟል፡፡

ይህንን አጭር አስተያየት እንድፅፍ ምክንያት የሆነኝ ናሽናል በተሰኘ ጋዜጣ ላይ ከሳምንት በፊት ያነበብኩትና ከላይ የተጠቀሰውን የቀድሞው መንግስት የተሳሳተ መስመር የሚደግፍ ዘገባ ነው፡፡ ዘገባው ኢትዮጵያ እየገነባችው የሚገኘው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የግብፅን ህዝብ ህልውና አደጋ ላይ ይጥላል የሚል የተሳሳተ መልዕክትን አዝሏል፡፡ እውነታው ግን ከዘገባው ፍፁም የተለየ ነው፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የህዳሴው ግድብን በተመለከተ በኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ በተለያዩ የውሃ ባለሙያዎች የተለያዩ መግለጫዎችና አስተያየቶችን ተከታትያለሁ፡፡ እንደእኔ አመለካከት ከእነዚህ መግለጫዎችና ሙያዊ አስተያየቶች መረዳት የሚቻለው የህዳሴው ግድብ የግብፅንም ሆነ የሱዳንን ህዝቦች ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል አይደለም፤ ይልቁንም አገራቱ ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ መልኩ የግድቡ ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ነው፡፡ አዲሱ ግብጽ መንግስትም ሆነ የሱዳን መንግስትም ከዚህ ያልተለየ አቋም ማራመድ የጀመሩበት ሁኔታ በስፋት እየተስተዋለ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ አካላት ሁሉ በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡ የህዳሴው ግድብ ከኢኮኖሚ ጠቀሜታው ባሻገር የአባይ ወንዝን በወጉ ከማስተዳደር ጉድለት የሚመነጩ ማህበራዊ ቀውሶችን ሊያስወግድ እንደሚችል የውሃ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል፡፡ የወንዙን ውሃ በአግባቡ ማስተዳደር አለመቻሉን ተከትሎ በተለይ በወንዙ ዳርቻና አካባቢ በሚኖሩት የሱዳንና ግብጽ ህዝቦች ላይ በየጊዜው የሚደርሰውን የጎርፍ አደጋ ያስቀራል፤ ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርገውንም ደለል ዘለቄታዊ መፍትሄ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱ አገራት ከግድቡ ከሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም ግድቡ የሶስቱ አገራት የጋራ ኃብት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ

አኳያ እንዲያውም ግብፅና ሱዳን ለፕሮጀክቱ ከሚያስፈልገው ወጪ ውስጥ የተወሰነውን የሚጋሩበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም በብዙዎች ዘንድ ተነግሯል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የዛሬ ዓመት የህዳሴው ግድብ መጀመርን ይፋ ባደረጉበት ወቅት እንደተናገሩት የግድቡ ግንባታ በአባይ ወንዝ አማካኝነት ግብጽንና ሱዳንን ለዘመናት ለጉዳት ሲዳርግ የኖረውን ደለልና እርሱንም ተከትሎ ይፈጠር የነበረውን የጎርፍ አደጋ በዘላቂነት ያስወግዳል፡፡

የህዳሴው ግድብ ግንባታ ለግብፅና ሱዳን የሚፈጥረው አዎንታዊ ሁኔታ እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ ግድቡ የወንዙን የውሃ መጠን በማሳደግ ረገድም ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወንዙ ውሃ ትነት አማካኝነት በተለይ በታችኛው የተፋሰሱ አገራት ዘንድ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የውሃ ብክነት ችግር የህዳሴው ግድብ ያስወግደዋል፤ ይህንንም ተከትሎ የወንዙ የውሃ መጠን ይጨምራል፡፡

ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ የመጠቀም ሙሉ መብት ያላት ቢሆንም ይህንን መብቷን ሌሎቹን የተፋሰሱ አገራት በሚጎዳ መልኩ ተግባራዊ የማድረግ ምንም ዓይነት ፍላጎት እንደሌላት በተለያዩ አጋጣሚዎች አስታውቃለች፡፡ እናም በህዳሴው ግድብ ግንባታ አማካኝነት በተለይ በግብፅና ሱዳን በኩል አንዳችም ቅሬታ ሳይነሳ በጋራ መግባባትና ተጠቃሚነት ላይ በተመሰረተ መርህ ስራውን ለመቀጠል የተለያዩ የዲፕሎማሲና ፖለቲካዊ ጥረቶችን አድርጋለች፤ በማድረግም ላይ ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ በወንዙ ላይ የጀመረችው የህዳሴው ግድብ በምንም መልኩ የግብፅንም ሆነ የሱዳን ጥቅም እንደማይጎዳ ከማረጋገጧም በተጨማሪ ይህንኑ በማጥናት ሪፖርት የሚያደርግ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲዋቀር በራሷ ተነሳሽነት ሀሳብ አቅርባለች፡፡ በኢትዮጵያ፣ በግብፅና በሱዳን እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የውሃ ባለሙያዎች አማካኝነት የተቋቋመው ይህ ኮሚቴ ስራውን መጀመሩን የሚዲያ ዘገባዎች አመልክተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያ መንግስት የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ ውስጥ በሊዝ መሬት ወስደው በሚንቀሳቀሱ ኩባንያዎች የመስኖ እርሻ አገልግሎት እንደማይውል በተደጋጋሚ አረጋግጧል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ውሳኔ ዓላማ በአገራቱ መካከል ግልፅነትን በመፍጠር በመተማመንና በመተጋገዝ ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር መሆኑን ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ የወሰደቻው እርምጃና እያሳየችው ያለው ቅንነት በግብፅም ሆነ በሱዳን መንግስታት ዘንድ አድናቆትን አትርፏል፡፡ በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር አብዱልራህማን ሲር አልከሂቲም ከአንድ የአገር ውስጥ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ  ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በግድቡ ግንባታ ዙሪያ ሱዳንን፣ ግብፅንና ኢትዮጵያን ያካተተ ኮሚቴ ተዋቅሮ በጋራ እንዲሰራ ሀሳብ

ማቅረባቸው  ከወንዙ ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ችግሮች በውይይት ለመፍታት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው በማለት አድንቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከወራት በፊት በግብፅ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት የግብፁ አቻቸው ኢሳም ሸረፍ፤ የህዳሴው ግድብ በሶስቱ አገራት የሚካሄዱትን የልማት ጥረቶች በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ ግድቡ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ግብፅንና ሱዳንንም ይጠቅማል ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳም ሸረፍ አረጋግጠዋል፡፡

የሱዳን ውሃ ኃብት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ሰይፈል ዲን ሃማድ ሰብደላህ በበኩላቸው የህዳሴው ግድብ በምክክርና መግባባት መርህ እውን ከሆነ ከኢትዮጵያ ይልቅ ሱዳንን እጅግ ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሶስቱ አገራት መካከል በጋራ ለመስራት የሚያስችል መሰረት ተጥሏል፡፡ እላይ ከተጠቀሱት እውነታዎች በመነሳትም የህዳሴው ግድብ የሶስቱ አገራት ህዝቦች የጋራ ኃብት ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው ብሎ መናገር አያዳግትም፡፡

በግብፅ ለተካሄደው ህዝባዊ ዓመፅ ምስጋና ይግባውና ዛሬ በኃይል እንጂ በድርድር የማያምነው አክራሪው የሙባረክ አስተዳደር ተገርስሷል፡፡ በዚህም ለአያሌ ዓመታት ከፍተኛ የውዝግብ ምንጭ ሆኖ እንዲኖር ምክንያት የሆነው እንቅፋት ተነስቷል፡፡ የግብፅን ህዝባዊ አመፅ ተከትሎ ስልጣኑን የተረከበው መንግስት ለህዳሴው ግድብ አዎንታዊ አመለካከትን እያሳለበተ ከመምጣቱም በላይ የቀኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶቹ ዙሪያ ከአባይ ተፋሰስ አባል አገራት ጋር ለመደራደር ከፍተኛ ዝግጁነት ማሳየት ጀምሯል፡፡

ይህም ኢትዮጵያን ጨምሮ የተፋሰሱ አባል አገራት የወንዙን ውሃ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም የሚቻልበትን ስርዓት ለመፍጠር የጀመሩትን በውይይትና ድርድር ላይ የተመሰረተ ሂደት እንደሚያጠናክረው በጉዳዩ ዙሪያ እውቀት ያላቸው ብዙዎች የሚሰጡት አስተያየት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከአባይ ውሃ ጋር በተያያዘ የሚነሱትን የሌሎች አባል አገራት የመብት ጥያቄዎች አዲሱ የግብፅ አስተዳደር የተቀበለበት መንገድ በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያውና እጅግ ገንቢ መሆኑንም ተንታኞች በመግለጽ ላይ ናቸው፡፡ በአዲስና የሰለጠነ አስተሳሰብ የሚመራው አዲሱ የግብጽ መንግስት ከሁሉም የተፋሰሱ አባል አገራት ጋር በመቀራረብ መስራት መጀመሩ በብዙዎች ዘንድ እንደታላቅ መልካም እርምጃ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ የተፋሰሱ አባል አገራትም ይህንን በግብፅ ዘንድ የሚታየውን አዎንታዊ እርምጃ አድንቀዋል፡፡ አንዳንዶቹም ይህንንም የሰላምና የድርድር መንገድ ለማበረታታት ይመስላል የውሃውን ፍትሃዊ የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተብሎ ዓመታት የወሰደ ውይይትን ተከትሎ

በስድስት የተፋሰሱ አባል አገራት የተፈረመውን የናይል ኢኒሽዬቲቭ ስምምነት በግብፅ በህዝብ የተመረጠ ህጋዊ መንግስት ስልጣኑን እስኪረከብ ድረስ በየአገሮቻቸው መንግስታት በማፀደቅ ህጋዊ ሰነድ የሚያደርጉበትን ጊዜ ለማራዘም ለግብጽ ባለስልጣናት ቃል ገብተዋል፡፡ ይህንን ቃል ከሰጡት የተፋሰሱ አባል አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡

ከዚህ አኳያ በተለይ በኢትዮጵያ የተወሰደው እርምጃ ውዝግቡን ከማርገብ አኳያ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው በካይሮ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የበርሃ ልማት ማዕከል ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ሪቻርድ ቱትዊለር ተናግረዋል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ “መለስ በኢትዮጵያ ጉብኝት ላደረጉት የግብፅ ልዑካን ቡድን የግብፅ የሽግግር መንግሥት ወደ ቋሚ መንግሥት እስኪቀየር የናይል ተፋሰስ ስምምነትን ማፅደቁን እናዘገየዋለን ማለታቸው በሁለቱ አገራት የነበረውን አወዛጋቢ ግንኙነት ለማብረድ አስችሏል፡፡” ከዚህም በተጨማሪ ይህ ኢትዮጵያ የገባችው ቃል ግብፅ ጉዳዮን በጥሞና እንድትመረምረው በቂ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑንም ግብፃዊያን በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡

የአባይ ወንዝ ውሃና የህዳሴው ግድብ ግንባታ ጉዳዮች በዚህ መልኩ በታላቅ መግባባትና መተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ እየረገበ ባለበት በአሁኑ ወቅት ግን የግብፅ መንግስትንና ህዝብ ስጋት ውስጥ የሚከቱ ጥቂት ድምፆች ከሚዲያው አካባቢ አልጠፉም፡፡ እነዚህን ድምፆች የሚያሰሙት ደግሞ ከጥቂት የቀድሞው የግብፅ መንግስት ባለስልጣናት ነው፡፡ በእነዚህ አካላት ከሚቀርቡት መሰረት የሌላቸው አስተያየቶች መካከል የህዳሴው ግድብ ግብጽን ለአደጋ ይዳርጋል፤ ግብፃዊያንን ለኤሌክትሪክ ኃይል እጦትና ለርሃብ ያጋልጣል የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ናሽናል የተሰኘው ጋዜጣ ከሳምንት በፊት ባቀረበው ዘገባ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ባለፈው ዓመት ይፋ በሆነው እቅድ መሰረት የሚካሄድ ከሆነ ግብፅ አደጋ ላይ ትወድቃለች፤ በግድቡ ግንባታ ምክንያት ዋና ዋና የሚባሉት የግብፅ ከተሞች ለውሃ እና ለኤሌክትሪክ እጥረት ይጋለጣሉ፤ በአጠቃላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ግብፃዊያን ለርሃብ ይዳረጋሉ ሲሉ ለ12 ዓመታት የግብፅ የውኃ ሀብትና መስኖ ልማት ሚኒስትር የነበሩት ዶክተር መሐሙድ አቡ ዛይድ መናገራቸውን አመልክቷል፡፡

የአክራሪው የቀድሞው ሙባረክ አስተዳደር አባል የነበሩት እኚህ ሰውና ሌሎች ጥቂት መሰሎቻቸው ተግባር በግብፅ ህዝብ ዘንድ አለመረጋጋትንና ስጋትን መፍጠር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱን አመለካከት የሚያራምዱት የቀድሞዎቹ የግብፅ ባለስልጣናት ኢትዮጵያ ግድቡ በምንም መልኩ የግብፅን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ለማሳየት እያደረገች ያለውን ጥረት ያገናዘበ ካለመሆኑም በተጨማሪ በምንም ዓይነት ተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ግድቡ የግብፅንም ሆነ የሱዳንን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲዋቀር ሀሳብ ያቀረበው ያለማንም ጎትጓች በራሱ ተነሳሽነት መሆኑን ማጤን

የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ግድቡ እነዚህን አገራት ለጉዳት የሚዳርግ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ይህ ኮሚቴ እንዲቋቋም ሃሳብ ታቀርባለች ብዬ አላምንም፤ ሌሎችን የሚጎዳ እቅዷንም ይፋ ታደርጋለች የሚል እምነትም የለኝም፡፡ እንደእኔ እምነትም ሆነ ማንም ቅን ልቦና ያለው ታዛቢ ሊቀበለው እንደሚችለው የኢትዮጵያ መንግስት ሀሳቡን ያቀረበው በግድቡ ግንባታ አዎንታዊ አንደምታ ዙሪያ ጠንከራ የራስ መተማመን ስላለው ነው፡፡

ኮሚቴው ጥናቱን በማካሄድ ላይ ነው፤ የመጨረሻው ውጤት ገና አልታወቀም፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ በግብፃዊያን ዘንድ ጥርጣሬን መፍጠር፤ ብሎም የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማሻከር የሚደረገው አፍራሽ ዘመቻ ለማንም የሚበጅ አይደለም፡፡ እነዚህ የቀድሞው ግብፅ መንግስት የተሳሳተ ፖሊሲ አቀንቃኞች የምር የግብፅ ህዝብ ጉዳይ የሚያሳስባቸው ከሆነ የዚህን የኮሚቴ የመጨረሻ የምርመራ ውጤት መጠበቅ ነበረባቸው፡፡

ላለፉት በርካታ ዓመታት ግብፅን የመራው የሙባረክ አስተዳደር ርዝራዥ የሆኑት ዶክተር መሐሙድ አቡ ዛይድ እና መሰሎቻቸው አሁን የተያያዙት ተግባር የማይሰራና የከሰረ መሆኑን ግብፃዊያን እየተገነዘቡ መጥተዋል፡፡

ግብፅን በጊዜያዊነት እያስተዳደረ የሚገኘው መንግስት የአባይን ወንዝ ውሃ በተመለከተ ያለፈው የአገሪቱ ስርዓት ይከተለው የነበረው መንገድ የተሳሳተ መሆኑን በይፋ ገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት ከሌሎቹ የተፋሰሱ አባል አገራት ጋር ጠንካራ የትብብር ግንኙነት በመፍጠር ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ታጥቆ ተነስቷል፡፡ ይህም የአገሪቱ ባለስልጣናት ባለፉት ወራቶች ባደረጓቸው የዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ በግብፅና ኢትዮጵያ መንግስታት ከወራሪች በፊት የተካሄዱት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ውጤታማ መሆናቸውን የሁለቱም አገራት መንግስታት አስታውቀዋ፡፡ ሚዲያዎች እንደዘገቡት በአሁኑ ወቅት በግብጽና ኢትዮጵያ  መንግስታት መካከል እየተስተዋለ ያለው መቀራረብ በሁለቱ አገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝ ጉዳይን በተመለከተ እየተከተለችው ያለው ፖሊሲ  የዲፕሎማሲያዊ ተሰሚነትን እንድትቀዳጅ እያደረጋት ነው፡፡ ተንታኞች እንደሚሉት ይህ አሁን ኢትዮጵያ የተቀዳጀችው ደረጃ በተለይ የቀድሞውን የግብፅ የውጭ ፖሊሲ በሚያመልኩት ዘንድ እንደ ስጋት ሊቆጠርም ይችላል፡፡ ያም ሆኖ ግን በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ያልተመሰረተ አስተሳሰብ በምንም መልኩ የማያዋጣና ከወንዙ ጋር በተያያዘ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ የማያስችል መሆኑን አያሌ የግብፅ ምሁራን ጭምር እያመኑበት መጥተዋል፡፡

በመሆኑም የሶስቱ አገራት ህዝቦች በጥላቻ ላይ ለተመሰረተው የቀድሞው የግብፅ መንግስት ባለስልጣናት አፍራሽ ዘመቻ ቦታ አይኖራቸውም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ መተማመንንና

ግልፅነትን ለመፍጠር በጀመረችው ጥረት በአሁኑ ወቅት የህዳሴው ግድብን በተመለከተ በግብፅም ሆነ በሱዳን ህዝቦች ዘንድ አዎንታዊ ምላሽ እየተስተዋለ ነው፡፡ ግድቡ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የግብጽና የሱዳን ኃብት ጭምር ስለመሆኑም በአገራቱ ህዝቦች ዘንድ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ ይህም በመሆኑ የእነዚህ አገራት ህዝቦች የህዳሴው ግድብን ለጋራ ልማት ከማሰብ በስተቀር ለጥፋት ድምፃች ጆሮ አይሰጡም ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡